ሰ/መ/ቁ.101277

መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ጳውሎስ አርሺሶ

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ተወካይ አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** ሚ/ር አቤቻንድ ፖፖትላል ሜታ ወራሽ ጠበቃ አቶ ታደሰ መንገሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፕራይቬታዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀድሞ ወረዳ 2 ቀበሌ 11 በአሁኑ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 271 የሆነ የቡና ማጠቢያና ማከማቻ መጋዘን ከነቢሮዎቹ ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰደብን ይመለስልን የሚል ነው፡፡ ኤጀንሲውም ጉዳዩን አጣርቶ በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ2(3) ድንጋጌ መሰረት ከአዋጅ ውጭ በቀላጤ የተወሰደ ንብረት በሚለው ትርጓሜ ስለሚሸፈን አቤቱታ የቀረበበት መጋዘን ከነቢሮዎቹ በመርህ ደረጃ እንዲመለስላቸው ሲወስን ንብረቱን ግን ተጠሪ የሚረከበው በተጨማሪነት ለተሰሩት ክፍሎች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ በሚያቀርበው ወጪ መሰረት ክፍያውን ሲፈጽም ነው በማለት መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ወስኗል፡፡ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተርም መጋቢት 28 ቀን 2004 ዓ/ም የውሳኔውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ለመንግሥት ቤቶች አጄንሲ ጽፏል፡፡ የመንግሥት ቤቶች አጄንሲ ይግባኝ ለፕራይቤታይዜሽን ቦርድ አቅርቦ ቦርዱም የአጄንሲውን ውሳኔ የሚያስለውጥ ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም በማለት ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥር 271 የቡና ማጠቢያና ማከማቻ መጋዘን ከነቢሮዎቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሰው ከጥቅምት 1 ቀን

1972 ዓ/ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለሸቀጦች ጅምላ ንግድ አስመጪ ድርጅት /ጅንአድ/በማከራየት አመልካች እያስተዳደረ የሚገኘውን ለተጠሪ ይመለስ በማለት የተወሰነው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ከተመረመረ በኋላ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲም ሆነ ቦርዱ አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲመልስ የወሰኑት አመልካች በክርክሩ ተጠርቶ በአግባቡ ተከራክሮ መሆን ያለመሆኑን እና በቤቶች ኤጀንሲ ስር ሆኖ የቆዬው የድርጅት ቤትና መጋዘን ለተጠሪ ይመለስ ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 7 አንጻር ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ ታህሳስ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ ተቃውሞና መልስ ያቀረበ ሲሆን ተቃውሞውም የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም የሚል ነው፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የውሳኔ ይዘት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ከመመርመሩ በፊት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፏል ወይስ አላለፈም? የሚለውን በቅድሚያ ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፕራይቤታይዜሽን ቦርድ ውሳኔ የሰጠው ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው በ8/9/2006 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም የይግባኝ ውሳኔ ከተሰጠ ከአንድ ዓመት ከአስራ አንድ ወር ከሰባት ቀን በኂላ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡ አመልካች ግን የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንስ ለፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ውክልና ታግዶ እንዲቆይ ካደረገ በኃላ የካቲት 25 ቀን 2006 ዓ/ም እግዱን ያነሳ በመሆኑ የይግባኝ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ከዚህ ቀን ጀምሮ ነው በማለት ተከራክሯል፡ ይህ ችሎት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አፈጻጸሙን አግዷል የተባለውን ለማጣራት ማኀደሩን በትዕዛዝ አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡ ኤጀንሲው ነሐሴ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጻፈው ደብዳቤ በኤጀንሲው ውሳኔ የተጠቀሰውን ቁጥር 271 የሆነውን መጋዘንና ቢሮዎች በአፈጻጸሙ መሰረት እንዲረከቡ በማድረግ ጅንአድ ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነባቸውን ቁጥር 006፣008/1 እና 008/2 የሆኑትን መጋዘኖች በሚመለከት በተለዋጭ ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ እስከምናሳውቅ ድረስ አፈጻጸሙ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ የሚል ነው፡፡በዚህ ደብዳቤ መሰረት መጀመሪያ ውሳኔ ያረፈበት ቤት አፈጻጸም አልታገደም፡፡ ይልቁንም ደብዳቤው ውሳኔ የተሰጠውን ቤት የፍርድ ባለመብት እንዲረከብ ፍርድ ቤቱ እንዲያደርግ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአመልካች የይግባኝ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ከ8/9/2006 ዓ/ም ጀምሮ ነው የሚለው ክርክር ከዚህ አንጻር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(4) እንደተደነገገው ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርበው አቤቱታ ውሳኔ በተሰጠ 90 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ለማቅረብ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካጋጠመ የሰበር አቤቱታው ከመቅረቡ

በፊት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 324 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የይግባኝ ማስፈቀጃ ማመልከቻ ቀርቦ ሊወሰን ይገባል፡፡ ይህ ባልተደረገበት ሁኔታ አመልካች ጊዜ ያለፈበትን የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ጭብጥ ተይዞ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የመልስ ልውውጥ ያደረጉ ቢሆንም የሰበር አቤቱታው የስነ ሥርዓት ግድፈት የተፈጸመበት በመሆኑ የክርክሩን ይዘት መመርመር ሳያስፈልግ የሰበር አቤቱታውን ሰርዘናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ያላቀረበ በመሆኑ የሰበር አቤቱታውን ውድቅ አድርገነዋል፡፡
2. የሰበር አቤቱታው መሰረዙን እንዲያውቅ የፍርዱ ግልባጭ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ይላክ፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ በተመለከተ የግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 28 ቀን 2007 የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡ የአከራካሪው ንብረት ማህደር በመጣበት አኳኋን ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ